# የደም ታሪክ አይደገምም!!

**ዋጋው ድረስ** 07-16-14

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎችና የመሪዎቹ ታሪክ ከጅምሩ እስከ ዛሬ በውስብስብና በምስቅልቅል ሂደት የተመላ ክስተት ነው፡፡ አንድ ሆነው ተነስተው በአንድነት የማይዘልቁበት፣ ተማምለው የሚከዳዱበት፣ በእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክር ተጠላልፈው የሚጣጣሉበት፣ የሽኩቻ፣ የንቁሪያ፣ የእርስ በእርስ መጠፋፊያ፣ በሴራ ፖለቲካ የተሞላ አንዱን ከሌላው ለመነጠል ሆን ተብሎ ሰፊ የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚካሄድበት እጅግ አሳፋሪና አሳዛኝ ታሪክ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ሆነው የፓርቲ ጥንስስ ከኢዙአ እና ኢዙና በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መነሻውን አድርጎ ጀምሮ ወዳጃሞቹ፣ ጓደኞሞቹ፣ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የተሻለ እድገትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንመሰርታለን ብለው የተነሱት፣ ለሁለት ተከፍለው በመርህ ተለያይተው ኢሕአፓና መኢሶንን በተለያየ ጎራ መሠረቱ፡፡ ጓደኝነታቸው ቀርቶ በፍጹም ጠላትነት ተፈራርጀው በጭካኔ እስከ መገዳደል አመሩ፡፡

ኢሕአፓ ከደርግ ጋር መሥራት አይቻልም ሲል በዚህም ሃሳብ በውስጡ ለሁለት ሲከፈል የከተማ ትጥቅ ትግል ወጣቱን ያስፈጀል የሚለው በአንድ ወገን የከተማ ትጥቅ ትግል መጀመር አለበት ባዩ በሌላ ወገን፣ ወደ ኋላ ላይ ተመልሶ ደርግ በጠላትነት የፈረጀው መኢሶን ደግሞ ከደርግ ጋር መሥራት ይቻላል ብሎ ቆመ፡፡

ኢህአፓ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍጹም ኮሚኒስት በሆነ የትግል መስመሩ የመሬት ላራሹንና የዴሞክራሲያዊ መብቶችን ጥያቄ እንዲሁም ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም የሚለውን ከ1966 በኋላ የነበረውን ሕዝባዊ ትግል የመራ፣ በተለይም በወጣቱም በአጠቃላይ በሕዝቡም ውስጥ በተለያየ አደረጃጀት ሥር መግባት፣ ማደራጀት፣ ዳር ከዳር አገሪቱን በአብዮት ማዕበል ማናወጥ የቻለ ፓርቲ ነበር፡፡

የዚያን ዘመኑ ወጣት በሌላው ዓለም እንደነበረው ወጣት ሁሉ ማርክስሳዊ ርዕዮትን ለታዳጊ አገራት ነጻነት እድገት አዋጪና መሪ ነው ብሎ እንደሚያምንበት ሁሉ የኢትዮጵያም ወጣቶች በማርክሳዊና ሌኒናዊ ርዕዮት ዓለም፤ በሩሲያው ሌኒንና የቦልሼቢክ ፓርቲ በኋላም በቻይናው አብዮትና በነ ማኦ ዜዱንግ፤ በነ ቼውንላይ፤ በቬቴትናሙ ሆቺሚን ትግልና የዲየንብየን ፉ ጦርነት ድል፤ በኩባው ፊደል ካስትሮና በአርጀንቲናዊው ቼ ጉቬራ፤ በቺሌው ሣልቫደር አየንዴ፤ በአፍሪካ የነጻነት ታጋዮች እነ ኔልሰን ማንዴላ፤ እነ ሣሞራ ማሼል፤ እነ አጉስቲኖ ኔቶ፤ በአሜሪካው ጥቁር የነጻነት ታጋይ ማርቲን ሉተር ኪንግ፤ በፓለስታይኖች ትግልና ቁርጠኝነት በሌሎችም እጅግ ያነበበ፤ የጠለቀ እውቀት ያለው፤ ለኢትዮጵያ አዋጪና አማራጩ የፖለቲካ ሥርዓት፤ የትግሉ መንገድ የትኛው መሆን አለበት ብሎ ይወያይ፤ ይከራከር፤ ይሟገት የነበረ ፖለቲካዊ ንድፈ ሃሳቡና ግንዛቤው የላቀና የመጠቀ ትንታግ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ነበር፡፡

ብዙዎች የዛሬዎቹ መላው የጠፉባቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁነኛ አመራሮች የዚያው ትውልድ አባላት የነበሩ ናቸው፡፡ ምቾት፣ ድሎት፣ ቅንጦት የማያውቁ፣ ከፍተኛ የእውቀትና የመጽሀፍ ማንበብ ፍቅር የነበራቸው፣ በተለይ የሚገኙ መጽሀፍትን እየተቀባበሉ እስኪነትብ ድረስ የሚያነቡ፣ በእጅም እየገለበጡ የሚያስተላልፉ፣ በሸራ ጫማና በካኪ ልብስ እየኖሩ እየተዋከቡ እየተሳደዱም፣ ለአገሬና ለሕዝብዋ የተሻለ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲመጣ፤ ከድህነት ተላቀው የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ፤ የሰለጠነች ዘመናዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እገነባለሁ ብሎ በቁርጠኝነት የቆመ፤ ሕይወቱን ሳይሳሳ የከፈለ ትውልድ ነበር፡፡ መጨረሻው ግን የማያምር ሆነ፡፡፡

የአንድ ታላቅ ባለ ራዕይ ትውልድ ጅምር ጉዞ በእልቂትና ጥፋት ተደመደመ፡፡ በኢሕአፓና በመኢሶን መካከል የነበረው የከፋ የጠላትነት ስሜት፤ በሌላው ላይ መዝመት፤ ስም ማጥፋትና መግደል፤ በኢሕአፓ መሪዎች መካከል የተፈጠረው መሠረታዊ የትግል አካሄድ ልዩነት መከፋፈል መፍጠሩና እንደገናም እርስ በእርስ መጠፋፋት፤ መኢሶን የደርግ አመራሮችን ማርክሲዝም አስተምሮ ሲያበቃ መጨረሻ በተፈጠረው የፖለቲካ ልዩነት ከደርግ መውጣትና በጠላትነት ተፈርጆ መመታቱ፤ ሌሎችም የተለያዩ ፓርቲዎች አንዱ ሌላውን ለመዋጥ በሚያደርገውጥረት መመታት፤ መጥፋትና መዋጣቸው የኢትዮጵያን ፖለቲካና የፖለቲከኞቹን ሥይወት ከሥር መሠረቱ አናግቶትና አበለሻሽቶ አጠልሽቶት አልፏል፡፡

በዚህ ሁሉ ውስብስብ፣ ቁልፍልፍና ጎምዛዛ አዳጋችና አሰልቺ ተስፋ አስቆራጭ ፍልሚያ ከሁሉ አሳዛኙ በግራም በቀኝም ተለያይተው የተጠፋፉት የተጋደሉት ደርግም የመታቸው ሁሉም በየፊናቸው ለአገርና ለሕዝባችን የተሻለ እናስባለን፤ የእኛ መስመር ይበልጣል ይሉ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡

የረገፈው ወጣትና መተኪያ የሌለው ምሁር ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆች ናቸው፡፡ ገዳይም ሟችም ኢትዮጵውያን ናቸው፡፡ የተጎዳችው የሐዘን ማቅ የለበሰችውም ኢትዮጵያ ናት፡፡ የዚህ ሁሉ ታላቅ አገራዊ ጥፋት መንስዔው የፖለቲካ ልዩነትን በሰለጠነ መንገድ ሕዝብና አገርን ማዕከል ባደረገ መልኩ ለመፍታት አለመቻል ነው፡፡ እኔ ያልኩት ካልሆነ፤ የእኔ የእኛ መንገድ ብቻ ነው ትክክል፤ ሌላው ለእኛ መንበርከክ፤ በእኛ ሃሳብ መገዛት አለበት አለበለዚያ ጠላት ነው ብሎ መፈረጅና ማሳደድ፤ የሀሳብን ልዩነት ማክበርና የተሻለ አማራጭ ካለ ማሳየት ሲቻል ከእኛ በሃሳብ የተለየ ባንዳ፣ ሰላይ፣ ቅጥረኛ ወዘተ ነው ብሎ መፈረጅ ያመጣው ችግር ነው፡፡

የግለሰብን ስብዕና ለመግደል እጅግ ከፍተኛ የፈጠራ ስም ማጥፋትና ዘመቻ ማካሄድ፤ ወረቀት መበተን፤ በፍጹም አምባገነናዊነት ሌላውን የመናቅ የመርገጥ አባዜ፤ የሌላውን ኢትዮጵያዊ መብት በመርገጥና በመጣስ ከእኔ ከእኛ በላይ ለኢትዮጵያ አሳቢና ተቆርቋሪ የለም ማለት፤ ሌላው ዜጋ በአገሩ ጉዳይ እንደማያገባው አድርጎ መውሰድ፤ ብዙ አንብበናል ብዙ እናውቃለን ለአገሪቱ የሚበጃት የእኛ መንገድ ብቻ ነው፤ ሌላው ምን ያውቃል የሚለው ዛሬም ያልበረደ እብሪት ውጤት ነው፡፡

እርስ በእርስ መናቆር፣ መናናቅና መወነጃጀል እስከ መጠፋፋት መሄድ፤ ነፍሰ ገዳይ እየገዙ ወንድም ወንድሙን ማጥፋት ወ.ዘ.ተ የኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን መሠረትና ማንነት እጅግ በክሎት ለውድቀት አብቅቷቸዋል፡፡

በሚገርም ሁኔታ ዛሬ ደግሞ የተሻለና ከትናንት ጥፋትና አገራዊ ውድቀት የተማረ ልዩነትን በውይይትና በመቻቻል የሚፈታ፤ ልዩነቱን በነጻነት ጠብቆና አክብሮ ለጋራ አገሩ በጋራ የሚሰራ ራዕይ ያለው ትውልድ እንዳይፈጠር እነዚህ የቀድሞ የመጠፋፋት ዘመን በቀልን ያነገቡ በእብሪት የተናጡ፤ ከውድቀታቸው ያልተማሩ፤ የረገፈው ትውልድ የማይፀጽታቸው አዛውንቶች ዛሬ የተተካውን ትውልድ በዚህ ክፉ ደዌያቸው በመበከል ብዙ ሥራ ከውነዋል፤ እየሰሩም ነው፡፡

የሚገርመው፤ ዛሬ የተተካው ወጣቱ ትውልድ ለአገር እድገት ልማት ብሎ ታላቅ መስዋዕትነት ሲከፍል የነበረው፣ የሞተው፣ የቆሰለው፣ የረገፈው፣ የተሰደደው ትውልድ ልጆች መሆናቸው ነው፡፡ ትናንት ከረገፈው ትውልድ የትግል አካሄድና ውድቀት ብዙ መማርና ትውልድ ማስተማር ሲቻል ዛሬ የተተካውን ባለ ወር ተራ ትውልድ በባዶ ሜዳ እያጀገኑ ወጣት ነህ ተነስ ምን ትጠብቃለህ እያሉት ነው፤ ለትውልድ ደም መፋሰስ እያነሳሱትና እየመረዙት ይገኛሉ፡፡

ያ ወንድም ወንድሙን፤ እህቱን፤ አባቱን በአስተሳሰብ በፖለቲካ ልዩነት የገደለበት፤ ድሀ ድሀ ወገኑን ያጠፋበት፤ ቆሻሻ አገርና ትውልድ ገዳይ ዘግናኝ ታሪክ ዛሬም በኢትዮጵያ እንዲደገም እነዚህ የበቀልና የመጠፋፋት ፖለቲካ አቀንቃኝ የሆኑ አዛውንት ፖለቲከኞች ወጣቱን እየጎተጎቱ ያክላላሉ፡፡

ትናንት በደርግ ዘመን የኢትዮጵያ ሠራዊት ከመላው የኢትዮጵያ ደሀ ቤተሰብ የተውጣጣ፤ ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር መከበር ታላቅ መስዋዕትነት የከፈለ፤ አገሬ ብሎ የሞተና የደማ፤ ከመሪዎች እስከ ታችኞቹ ክፍል፤ ሐብቴ፣ ንብረቴ የሚለው ምንም የሌለው መሆኑን ያውቁ የነበሩት አብዛኞቹ ምሁራን ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያምና ብዙዎቹ፤ የፋሽስት ሠራዊት ስለሆነ መፍረስ አለበት እያሉ እንግሊዝና አሜሪካ እየዞሩ ሲቀሰቅሱ እንዳልነበር ሁሉ ዛሬም ደግሞ በአዲስ መልክ የተደራጀና በድሀ ኢትዮጵያውያን ልጅ የተገነባውን አገሪቱን ዳር ከዳር የሚያስከብር፤ ሕይወቱን ሰጥቶ የቆመውን የመከላከያ ሠራዊት፤ ፖሊስ ፌደራሉን፤ ደህንነቱን፤ የገዢው ፓርቲ አገልጋይ ስለሆነ ታማኝነቱ ለሕዝብ ሳይሆን ለሥርዓቱ ነው፤ የሕዝብ አይደለም እያሉ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ምሁራን እንዲህ አገሪቱን በየሥርዓቱ የሚያምሱበት፤ ሕዝብን የማያናቁሩበት፤ ተከታታይ ሥርዓት ባለው መንገድ ታሪክና ባህል ተጠብቆ የዛሬው የጥንቱን አክብሮት እንዳይሄድ፤ ሊያባሉንና ሊያጠፋፉን የሚሞክሩበት ከታሪክ የማይማሩበት ምክንያት ምንድነው? ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ፤ መንግሥት አልፎ መንግሥት ሲመጣ፤ የኢትዮጵያ ታሪክም የገነባችውም እየተናደ፤ እየፈረሰ እንደገና ዳዴ ብላ በጨለማ በእንፉቅቅ እንድትነሳ፤ አዲስ የሚመጣው የትናንቱ ታሪክ እንዲያጠፋው፤ እንዳያወድመው የኢትዮጵያ ምሁራን ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ሁሌም የሚመኙት ምንድነው የተደበቀው ሚስጢራቸው?

ወይንስ እኛ ካልመራናት ኢትዮጵያ የምትባል አገር ሠላም አግኝታ ለምታ አድጋ ተሻሽላ ሰልጥና ማየት አንፈልግም ነው? ወይንስ እኛ ካልመራነው በኢትዮጵያ ታሪክ የተመዘገበውን፣ ታላቅ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እንዲሁም የዲፕሎማሲ ግዙፍ የጉዞ ታሪክ በተጨባጭ የሚታየውን አናውቅም አንቀበለውም ነው፡፡ የአገር ልማት እድገት ሁሉንም ዜጋ ሊያኮራና ሊያስደስት ይገባል እንጂ እንዴት ተደርጎ ያስከፋል? ዛሬ የተሰራው ሥራ ለተከታታይ ትውልድ የሚያልፍ፣ ዝንተ ዓለም የሚጠቀስ እንጂ መቼም አንገት አያስደፋም፣ ሰዎች ምንነካቸው ምንድነው የምሁርነት የኢትዮጵያዊነት መገለጫ? ደም የጠማውና የተክለፈለፈ የቀትር አጋንንት ይመስል የድሀውን ልጅ በቀልና ጥላቻ እየጋቱ በስሜታዊነት እየቀሰቀሱ፣ ለእነሱ የሥልጣን አራራ ሲሉ ደም እንዲከፍል፣ ደሙ እንዲፈስ የሚሹት ለምንድነው?

ነገ የት ነህ ብለው ዘወር ብለው እንደማያዩት የትናንቱ ትውልድ ምስክር ነውና ጥለውና አጋፍጠውት፣ ባህር ማዶ አውሮፓና አሜሪካ መሄዳቸውን ኑሯቸውን ውጪ አገር አድርገው ዜግነትም አግኝተው የተቀናጣ ኑሮ እንደሚኖሩም ያውቃልና የድሀው ሕዝብ ልጅ ለእነዚህ የበቀል ፖለቲካ ሴረኞች መገበሪያ አይሆንም፡፡ እነሱን ሰምቶና ተደልሎ እሣት ውስጥ አይማገድም፡፡

## ደም መፋሰስ በቃን!!

ያኔ በኢሕአፓ ውስጥ የነበረው አመራር በአክራሪ ጽንፈኞችና በሌላም በኩል በእውቀት መጥቀው ፖለቲካውን መረዳት በቻሉ እጅግ ብስልና ዘመናዊ አስተሳሰብ ባላቸው ወጣቶች መካከል ደርግን እንዴት እንታገለው በሚለው አካሄድ ሁለት ቦታ ተከፍለው ነበር፡፡

ጽንፈኛውና አክራሪው ኃይል ደርግን ለመምታት የከተማ ትጥቅ ትግል መጀመር አለብን ሲል ሞደሬት ዘመናዊ አሰተሳሰብና ልቀት የነበራቸው ሁለት የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራሮች ብርሐን መስቀል ረዳ እና ጌታቸው ማሩ ደግሞ ወጣቱን እናስፈጀዋለን፣ የከተማ ትጥቅ ትግል አያዋጣም ከተማ ውስጥ መግደል ብንጀምር ደርግ በመላው አገሪቱ በኢሕአፓ ወጣቶች ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ያካሂዳል ብለው ተከራከሩ፡፡

ጽንፈኛውና አክራሪው የኢሕአፓ አመራር ብርሐነ መስቀል ረዳንና ጌታቸው ማሩን አወገዘ፣ ኮነነ፣ ፓርቲውን በመከፋፈል በአንጃነት ፈረጃቸው፡፡ በመጠለያ ቤት በኢሕአፓ

ሰኳዶች እየተጠበቁ እስረኛ እንዲሆኑ አደረገ፤ አክራሪው አመራር ሽጉጦች ከያለበት በማሰባሰብ ወታደራዊ ትምህርት የሰለጠኑ ስካዶች በማሰማራት በደርግና በመኢሶን አባላት በቀበሌ ተመራጮች፤ በድህ አብዮት ጠባቂዎች ላይ ሳይቀር በተለያየ ቦታዎች ግድያ አካሄደ፤ በዚህ የተበሳጨው ደርግ ኢሕአፓን በአናርኪስትነት በመፈረጅ በአንድ አብዮታዊ ሞት የሺህ አናርኪስቶች ሕይወት ይመነዘራል በሚል መፈክር ኢሕአፓን ለማፈራረስና ለማጥፋት ይፋ ጦርነት ከፈተ፡፡

የቀን ከለሊት አሰሳ ብቻ ሳይሆን አገሪቱ በተለይ የጦርነት አውድማ ሆነች፤ እጅግ…እጅግ ብዙ ሊሰሩ ይችሉ የነበሩ ታላላቅና ብሩህ አዕምሮ የነበራቸው ምሁራንና ወጣቶች በጥይት ተፈጁ፤ ኢሕአፓም መግደል እስከቻለችው ድረስ ገደለች፤ የማይመጣጠን ኃይል፣ አቅምና ድርጅት ካለው ከተደራጀ ሠራዊት ጋር የገጠመው ፍልሚያ መሠረታዊ የታክቲክና ስትራቴጅ ስህተት ስለሆነ አክራሪውና ጽንፈኛው የኢሕአፓ አመራር አንድ ታላቅ ባለራዕይ ትውልድ እንዲረግፍ ቅስሙ እንዲሰበር አደረገ፡፡ ለምን እልቂት ይመጣል፤ ወጣቱን ለምን እናስፈጃለን ያለውን የራቀ አዕምሮ የነበረውን ጌታቸው ማሩን በገዛ ጓደኞቹ ከታሰረበት የጀርባ አሰሳ ሲመጣ ለማምለጥ ሲሞክር የራሱ ጓዶች በጥይት ደብድበው ገደሉት፤ የአረመኔ አረመኔነት መልኩ እንዳይታወቅ ከሞተ በኋላ ጋዝ አርከፍክፈው አቃጠሉት፤ ብርሐነ መስቀል ረዳ እና ጌታቸው ማሩ ትውልድ አናስጨርስም በሚለው አቋማቸው፤ በብስል እውቀታቸው ሐውልት ሊቆምላቸው የሚገባ፤ መቻቻልን ያስተማሩ፤ የፖለቲካ ልዩነትን በውይይት መፍታት አለብን ብለው በያዙት አቋማቸው መስዋዕትነት የከፈሉ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡

አክራሪና ጽንፈኛ አቋም ግትርነት፤ የከፋ ጥላቻ፤ ስሜታዊነት፤ ጀብደኝነት፤ ለአንድ ትውልድ እልቂት ሁነኛ ምክንያት ሆነ፡፡ ይኼ ከበቂ በላይ ዛሬም ላሉት አክራሪና ጽንፈኛ ፖለቲከኞች ታላቅ ትምህርት ሊሆናቸው ይገባ ነበር፤ እነሱ ግን አድሮ ቃሪያ፤ አድሮ ጥጃ እንዲሉ ዛሬም አዲስ የተተካውና ስለትናንት ፖለቲካ ምንም የማያውቀውን ትውልድ ጥላቻ እያስተማሩ በቀል እያወረሱ ገለህ ሙት ለመተላለቅ ተነሳ እያሉት ነው፡፡ የትውልድም የአገር ጠንቅም ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ስንት ጊዜ፤ ስንት ዘመን፤ ስንት ትውልድ፤ የገዛ ልጆችዋ ጠላት ሆነዋት እርስ በእርስ እየተባሉ፤ እየተላለቁ፤ እየተጠፋፉ፤ ራሳቸውም ጠፍተው አገርን፣ ሕዝብን፣

ታሪኳንም እየገደሉ እንዴት ትደግ፤ ሌሎች አገራት ከደረሱበት ደረጃ እንዳትደርስ እየተደረገ ወይንም እያደረጉ ስንት ዘመንስ ይቀጥላሉ?

የቀደሙ አባቶች እርግማንስ ይሆን? በእብሪት፤ በማን አለብኝነት፤ ከእኔ ከእኛ በላይ ኢትዮጵያዊ የለም በሚል ድንቁርና፤ ለአገር ሲባል አንድ ሆነው ተነስተው ሲከፋፈሉ፣ ሲበታተኑ፣ ጎራ ለይተው ሲቆሙ፣ እንደገናም 30 እና 40 ፓርቲ ሲመሰርቱ፣ በየፊናቸውም ሕዝቡንና ተተኪውን ወጣት ትውልድ ሊቀራመቱት፤ የደም ዋጋ ሊያስከፍሉት፤ ሲዋትቱ ይህች አገር እነዚህን የልጅ ጠላቶች ተሸክማና አዝላ እስከ ስንት ዘመን ታነክሳለች?

የድሮ አባቶች ፕሮፌሰር፤ ዶክተር ሳይሆኑ፤ ማስትሬት፣ ዲግሪና ዲፕሎማ ሳይኖራቸው በተፈጥሮ አስተዋይነትና ብልህነታቸው ሁሉን ዳር ከዳር አስማምተው፤ አቻችለው፤ አፋቅረውና አወዳጅተው፤ አዋደውም ጭምር በአንድነት አጽንተዋት የሄዱትን አገር በተጀመረው መንገድ የበለጠ ጠብቆ ማሳደግ ሲገባ ጽንፈኛ ተቃዋሚው በአመጽ፣ በሁከትና ብጥብጥ ልናጣት ላናውጣት የሚልበት፤ የአገርና የሕዝብ ፍቅር ነው ወይንስ ጥላቻ? ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ከነበረችበት አዘቅትና ድህነት ለማውጣት ጠንክሮ ሰርቷል፤ ለውጧታልም፡፡ በአፍሪካም በዓለምም የተለየ የክብር ቦታ እንድታገኝ፤ ስምዋ እንዲቀየር፤ ክብር እንዲያገኝ ሰርቷል፡፡ የዓለም ኃያላን መንግሥታት፣ ለጋሾችና ተቋማት ኢትዮጵያ ለሁሉም ወዳጅ እንጂ ለማንም ጠላት አይደለችም በሚል ፖሊሲ ምሥራቅ ከምዕራብ ሳይል መልካምና በጎውን ለኢትዮጵያ የሚጠቅመውን ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት ችሏል፡፡

በዚህም በዓለም በፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ከሚገኙት አገሮች ተርታ መሰለፍ ችላለች፡፡ የተሰሩት ታላላቅ አገርንና ሕዝብን በመሠረታዊ መልኩ የለውጡ ሥራዎች ሁሉ የዛሬውም ተከታታዩ የኢትዮጵያ ትውልድም የሚኮራባቸው ቋሚ ሐውልቶች ናቸው፡፡ አለመታደል ሆኖ ይህን ሁሉ የሚያጣጥል፤ ጥላሸት የሚቀባ፤ በጥላቻና በስሜታዊነት የተዋጠ፤ በወሬና በአሉባልታ የናወዘ፤ የጥፋት ሕልም ነግቶ እስኪመሽ የሚያልም ተቃዋሚ ነው ያለን፡፡ ኢትዮጵያ የዓረቡ አለም የጥፋት አብዮትና የእልቂት ሽብር ተውኔት ማራገፊያ ወደብ አይደለችም፡፡ ይህ የፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች አገሪቱ ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖራት፤ ከድህነት፣ ከተረጂነት እንዳትወጣ፤ ሠላም አግኝታ ወደ ልማትና እድገት እንዳታመራ በተለያየ ዘመናት የራሷን ልጆች በጥቅም እየገዙ በጠላትነት ሲያሰልፉባት ኖረዋል፡፡ ዛሬም ከዚህ ሴራቸው አልታቀቡም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ለዚህ ሥውር ሴራ አይንበረከክም፡፡ ልጆቹንም መገበሪያ አድርጎ አይሰጥም፡፡ ከእንግዲህ ኢትዮጵያ የጀመረችውን ታላቅ የልማትና የኢኮኖሚ እድገት ጉዞ አጎልብታና አጠናክራ ትቀጥላለች፡፡ የጥፋት ኃይሉ ለአገርና ለሕዝብ በመቆርቆር ስም ጭርሱኑም ወደ ገደል ሊወስዳት እየተጣደፈ በመሆኑ በሠላማዊነት ስም ተሰልፈው ተቃዋሚ ነን ለሚሉና ሰልፋቸውን ከአመጽና ከነውጥ ጋር ላቀናጁ ኃይሎች አገሪቱ የምትሰጠው ጊዜ የላትም፡፡ በሠላምና ሠላማዊ መንገድ ብቻ የሚሰሩት ህገ መንግሥታዊ መብታቸው እንደተከበረ ይቀጥላሉ፡፡ እነሱም ለአገሪቱና ለሕዝቡ ሠላም ያላቸውን ቁርጠኝነትና አቋም በተግባር መግለጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የግሉን ፕሬስ መጽሄቶችና ጋዜጦች በዋነኛ ልሣንነት በመጠቀም በከፍተኛና ሥውር የገንዘብ ኃይል በመርዳትና በማደራጀት የጥላቻና የአመጽ መልዕክቶች ለሕዝብ በማዳረስ የአገሪቱን ሠላም ለማደፍረስ የሚደረገው ጥረት በአገርና በሕዝብ ሠላምና መረጋጋት፣ ደህንነት ላይ ያነጣጠረ ታላቅ ወንጀል ነው፡፡ የእልቂትና የመበላላት የደም መፋሰስ ታሪክ በኢትዮጵያ ከእንግዲህ አይደገምም!!